# የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ

2007 ዓ.ም

# መመሪያ ቁጥር 02/2003 ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን የዓላማ ማስፈፀሚያና አስተዳደራዊ ወጪዎችን ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 02/2003 ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች

ሀ/ የኤች.አይቪ ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ የሚገኙ ወገኖችን ተጠቃሚነት ለማጎልበት የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ ሥር የሚካተቱ ተጨማሪ የወጪ ርእሶች፡-

- ተቀጣሪ ሆኖ ሲሰራ ለግለሰቡ የሚከፈል የደመወዝ ወጪ፣
- እንክብካቤና ድጋፍን የሚሰጡ ሞግዚት ተንከባካቢዎች የደመወዝ ወጪ፣
- ቤት ለቤት እየተዘዋወሩ ድጋፍን የሚሰጡ ተቀጣሪ ሠራተኞች የደመወዝ ወጪ፣
- ወላጆቻቸውን በኤች.አይቪ ኤድስ ያጡ ህፃናትን በማሳደጊያ ማእከል ለህፃናቱ ጤናማ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ እድገት ድጋፍና ክትትልን ያደርጉ ዘንድ የመደቧቸው ቋሚ ተቀጣሪ የጤና ባለሙያዎች የደመወዝ ወጪ፣

# መመሪያ ቁጥር 02/2003 ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች ---የቀጠለ

ለ/ የአካል ጉዳተኛ ወገኖችን ተጠቃሚነት ለማጐልበት የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ አውድ ሥር የሚካተቱ ተጨማሪ የወጪ ርእሶች፡-

- ተቀጣሪ ሆኖ ሲሰራ ለግለሰቡ የሚከፈል የደመወዝ ወጪ፤
- በተለየ ሁኔታ የተሰራ ተሽከርካሪ ግዥን ሲፈፅም የተሽከርካሪው ግዥ ወጪ እና ተሽከርካሪው አገልግሎት ሲሰጥ የሚያስፈልጉት የነዳጅ የተሽከርካሪው ማለሳለሻ ቅባቶችና የጥገና ወጪዎች፤
- ለአካል ጉዳተኞች እንክብካቤና ድጋፍ ይሰጡ ዘንድ የመደቧቸው ረዳቶች ቋሚ ተቀጣሪ ከሆኑ የሠራተኞቹ የደመወዝ ወጪ፤
- ለአካል ጉዳተኛ እንክብካቤና ድጋፍን የሚሰጡ ሞግዚቶች ተከባካቢዎች የደመወዝ ወጪ፤
- ቤት ለቤት እየተዘዋወሩ እንክብካቤና ድጋፍ የሚሰጡ ቋሚ ተቀጣሪ ሠራተኞች የደመወዝ ወጪ፤
- በአካለል ጉዳተኞች ዙሪያ ብቻ ታልሞ ለሚቋቋም ማሰልጠኛ ተቋም የሚወጣው ወጪ፤
- በቅጥር ግቢ ውስጥ ለአካል ጉዳተኞ ወገኖች ተደራሽነትና ምቹነት ሲባል የሚገነባ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ግንባታ ወጪ፤

# መመሪያ ቁጥር 02/2003 ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች ---የቀጠለ

ሐ/ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል እና ከንፅህና አጠቃቀም አንፃር የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ አወድ ሥር የሚካተቱ ተጨማሪ የወጪ ርእሶች፡-

- የንፁህ መጠጥ ውሃን ለማጎልበት ይረዳው ዘንድ የሚፈፅማቸው የጉድጓድ ውሃ መቆፈሪያ መሳሪያ ተሽከርካሪ /መሸን -ሪግ/ ግዥና ተሽከርካሪው አገልግሎትን ሲሰጥ የሚያስፈልጉት የነዳጅ ፣ የተሽከርካሪ ማለስለሻ ቅባቶችና የጥገና ወጪዎች እንዲሁም በዚሁ ተሽከርካሪ ላይ ተቀጥሮ የሚሰራው ተሽከርካሪ ሹፌር /ኦኘሬተር/ የደመወዝ ወጪ፣
- የንፁህ መጠጥ ውሃን ለማዳረስ የተገነቡ እንደ ቦኖ ውሃ ያሉ የመጠጥ ውሃ ማከፋፊያዎችን ይቆጣጠሩና ይጠብቁ ዘንድ የቀጠሯቸው ወይም የመደቧቸው ሠራተኞች ደመወዝ ወጪ፣
- የፈሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻን ለማስወገድ ሥራ ይውሉ ዘንድ የፈፀማቸው የተሽከርካሪ ግዥ ወጪዎች ፣ ተሽከርካሪው ማለስለሻ ቅባቶችና የጥገና ወጪዎች ወይም ድርጅቱ የፈሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻን ለማስወገድ ተሽከርካሪዎችን ተከራይቶ የሚጠቀም ከሆነ የተሽከርካሪዎች ኪራይ ወጪ የፈሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻን ለማስወገድ ያሰማሯቸው የጉልበት ሠራተኞች የደመወዝ ወጪ፣

# መመሪያ ቁጥር 02/2003 ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች ---የቀጠለ

መ/ የተፈጥሮና የአካባቢ አየር ጥበቃ እና የአየር ንብረት ለውጥ ሥራዎችን ለመደገፍ ሲባል የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ አውድ ሥር የሚካተቱ ተጨማሪ የወጪ ርእሶች:-

- በቀጥታ በመስክ ሥራዎችን የሚሰሩ ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች ደመወዝ ወጪ፣
- የደን ጥበቃ ሥራ ላይ የተሰማሩ ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች ደመወዝ፣
- ችግኝ ለማፍላትና ለማጓጓዣ የሚደረገው አጠቃለይ ወጪ
- ለአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ የሚውሉ የውሃ ማቆር ተግባራት የሚያስፈልጉ የተለያዩ ቁሳቁሶች እና መሣሪየዎች ግዥና ወደ አርሶና አርብቶ አደሮች የማጓጓዣ ሥራ የነዳጅና የተሽከርካሪ ማለስለሻ ቅባቶች ወጪ ወይም በመከራየት ለተጠቃሚዎች የማይደርሳቸው ከሆነ የኪራይ ወጪዎች

# መመሪያ ቁጥር 02/2003 ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች ---የቀጠለ

ሰ/ የግብርና ሥራዎችን ለመደገፍ ሲባል የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ አውድ ሥር የሚካተቱ ተጨማሪ የወጪ ርዕሶች፡-

- የምርጥ ዘር ግዥና ወደ አርሶ አደሮች የማጓጓዣ ለቴክኖሎጂ ሽግግር አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ማለትም ማዳበሪያ እና ለመስኖ ሥራ የሚያገለግል መሣሪያዎች ግዥና አቅርቦት እና ወደ አርሶ አደሮች ለማጓጓዝ የሚወጡ /በራሱ ተሽከርካሪ ከሆነ የነዳጅና የተሽከርካሪ ማለስለሻ ቅባቶች ወጪ ወይም በመከራይት ለተጠቃሚዎች የሚያደርሳቸው ከሆነ የተሽከርካሪ ኪራይ ወጪዎች

# መመሪያ ቁጥር 02/2003 ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች ---የቀጠለ

ረ/ የአቅም ግንባታና የስልጠና ተግባራትን ለመደገፍ ሲባል የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ አውድ ላይ የሚካተቱ ተጨማሪ የወጪ ርእሶች፡-

- በመመሪያ ቁጥር 02/2003 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአሰልጣኝ ስልጠና ተሳታፊዎች በተለይም ከተጠቃሚው ማሕበረሰብ ጋር በቀጥታና በቅርበት የሚገኙ በቀበሌና ተመሳሳይ የአደረጃጀት መዋቅር እርከን የሚሰሩ ባለሙያዎች እና ግንባር ቀደሞች /ሞዴሎች/ የሥልጠና ወጪዎች
- በመመሪያው ቁጥር 02/2003 ላይ በልዩ ሁኔታ ደመወዛቸው በዓላማ ማስፈፀሚያ እንዲካተት የተደረጉ ባለሙያዎችና ሠራተኞችን ለማሰልጠን የሚወጣ አበል ፣ የስልጠና ቁሳቁሶችና ጥራዞች ህትመት መጪዎች፡-

# መመሪያ ቁጥር 02/2003 ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች ---

ሽ/ የግንባታ ተግባራትን ለመደገፍ ሲባል የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ አውድ ስር የሚካተቱ ተጨማሪ የወጪ ርእሶች:-

በመመሪያው ቁጥር 02/2003 ላይ ለተጠቃሚዎች አገልግሎት የሚውሉ የግንባታ ሥራ ወጪዎችን አስመልክቶ በመመሪያው በእያንዳንዱ ክላስተር የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው

- ለተጠቃሚዎች የግንባታ አገልግሎት የሚውሉ የተፈጥሮ የግንባታ ግብአቶች /ድንጋይ ፣ አሸዋና የመሳሰሉትን/ የግዥና አቅርቦት ማጓጓዣ ወጪ የኢንዱስትሪያል ቁሳቁሶች ግዥና አቅርቦት ማጓጓዣ ወጪ /በራሱ ከሆነ የነዳጅና የተሽከርካሪ ማለስለሻ ቅባቶች ወጪ ወይም በመከራየት ወደ ግንባታ ቦታዎች የሚያደርሳቸው ከሆነ የተሽከርካሪ ኪራይ ወጪ/
- የሥራ ቦታቸው ግንባታቸው በሚከናወንበት ስፍራ ሆኖ በግንባታው ላይ በቀጥታ የሚሳተፍ የጉልበት ሌሎች የግንባታ ሥራ ተቀጣሪ ሠራተኞች ደመወዝ ወጪዎች፣
- ግንባታው በኮንትራት ለተቋራጭ ስራ የሚሰጥ ከሆነ የግንባታው የ70/30 በመቶ ድርሻ ተሰልቶ መግባባት መድረስና ውል ማሰር ያስፈልጋል፡፡

# መመሪያ ቁጥር 02/2003 ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች ---የቀጠለ

ቀ/ በመመሪያው ቁጥር 02/2003 ላይ አሻሚ ሆነው የተገኙ ድንጋጌዎች ላይ የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን ወይም የልማት ጣቢያ ወኪሎችን በተመለከተ:-

- መመሪያ ቁጥር 02/2003 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ "የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች" በሚል የተገለፁት የአዝርእት ባለሙያ ፣ የመስኖ ባለሙያ ፣ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ባለሙያ ፣ የእንስሳት ባለሙያ ወይም ከነዚህ ከተዘረዘሩት ሙያዎች ጋር ተመጣጣኝ ክህሎትን ይዘው በተመሳሳይ ደረጃ የሚሰሩ ባለሙያዎችን ማለት ነው፡፡
- በሌሎች ዘርፎች ሆነው ተመሳሳይ ደረጃና የሥራ ቦታ ያላቸው የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፡፡

## መመሪያ ቁጥር 02/2003 ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች ---የቀጠለ

በ/ የመጓጓዣ ወይም ትራንስፖርት ወጪን በተመለከተ፡-

- በሁሉም ዘርፍ የሚሰሩ ለተጠቃሚዎች የሚያደርጓቸው የምግብ ፣ የልብስ ፣ የመድኀኒት ፣ የትምህርት መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች እና የተለያዩ ቁሳቁሶች የማጓጓዣ ወጪዎች በራሱ ተሽከርካሪ የነዳጅና የተሽከርካሪ ማለስለሻ ቅባቶች ወጪ በመከራየት ከሆነ የተሽከርካሪ ኪራይ ወጪን የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ አውድ ሥር ይካተታል፡፡

# አመሰግናለሁ

